# Ethiopians Must Garner A Higher Form of Unity in Light of Kebede Michael Vision

**Ghelawdewos Araia**
**December 27, 2011**

This essay is intended to further reach out Ethiopians at home and in the Diaspora in an effort to emancipate themselves from narrow ethno-politics that has virtually gripped the minds of political groupings, apparently vocal and avowed opposition but that altogether lacks unity.

The lack of unity among Ethiopian opposition groups, as I have indicated several times elsewhere, boils down to 1) lack of higher level of political consciousness among the average Diaspora groupings; 2) lack of vision among the so-called leaders of the Diaspora opposition; 3) a diminished national and patriotic commitment as opposed to the forefathers who fought gallantly to preserve Ethiopian sovereignty and independence; 4) inability of Ethiopians to transcend their narrow ethnic affiliation and foster an all-Ethiopia agenda; and 5) willingly promoting ethnic associations that precludes a higher form of Ethiopian unity.

In order to overcome the above problems thus, I am inviting Ethiopians, wherever they may be, to carefully read the vision of Kebede Michael and seriously consider the current prevailing narrow and annoying hate politics. There are hundreds of Ethiopian visionaries as I have noted in my article entitled *Saluting the Wonderful Ethiopian Intellectuals*, but I have chosen Kebede Michael for this particular essay because I am concerned about the increasingly eroded unity of Diaspora Ethiopians and Ethiopia's genuine transformation for the better. Moreover, Kebede Michael uniquely combines both patriotism and development vision as demonstrated in his book, *How Japan Became Civilized* (**ጃፓን እንደምን ሠለጠነች**)

For those young Ethiopians who were born in the Diaspora and who could not read and write Amharic, I am earnestly asking their parents to translate the following excerpts from Kebede Michael's book:

**እንግዴህ የጃፓንን ታሪክ አንብበን ከጨረስን በኋላ እንደኛ በሥልጣኔ ወደ ኋላ ቀርቶ የነበረው ይህ ሕዝብ ቆራጥ በሆነ መንፈስ ተነሥቶ ይህን ሁሉ ሥራ በመሥራቱ አገሩን ከፍ አድርጎ ከትልቅ ቦታ አደረሳት ፣ እኛሳ ላገራችን የሚጠቅም ሥራ ለመሥራት ምን ማድረግ ይገባናል? የሚል አሳብ ከፊታችን መደቀኑ የማይቀር ነገር ነው።**

**ይልቁንም በኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም መንግሥት ጀምሮ ዝስካሁን ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ነገሥታት የነበራቸውን ችግር እየተመለከትን ፡ ያገራቸውንና የሕዝባቸውን ነፃነትና ክብር ጠብቀው ለመኖር የገጠማቸውን ፈተናና ትግል በእንዴት ያለ ድካምና ብርታት አሸንፈው ዛሬ እኛ የምንኮራበትን መብት**

እንዳወረሱን ስንመረምረው፡ ጃፓኖች ለነፃነታቸው ጥበቃ በየዘመኑ ከሠሩበት የጀግንነት ሥራ ጋር በጣም ይመሳሰላል። ነገር ግን የአውሮፓ ሥልጣኔ በዓለም ላይ እየተስፋፋች ሄዳ ወደ ኢትዮጵያና ወደ ጃፓን አገሮች ባንድ ዘመን ከገባች በኋላ ጃፓኖች ዘመናችን የፈጠረውን አዲስ የጥበብ መንፈስ በሚያስደንቅ ቅልጥፍና ተቀብለው ከባሕርያቸው ጋር ስላዋሀዱት በቅጽበት ተወርውረው ከታላላቆች መንግሥታት ጋር እኩል ሆኑ። ኢትዮጵያ ግን በዚህ በኩል ዳተኛ ሆና በመገኘቷ አውሮፓውያን አገርዋ ከገቡ በኋላ የሥልጣኔ ጥበቦች ሳትወርስ ስለዘገየች ያፄ ቴዎድሮስ፡ ያፄ የሐንስና ፡ ያጼ መኒልክ ዘመናት በከንቱ አለፉ፡ በእነዚህ ዘመናት ጠንክራ ሠርታ ቢሆን ኖሮ አሁን ያለፈው የፋሺስት የወረራ አደጋ ባልደረሰባት ነበር።

አሁንም አገራችን ኢትዮጵያ ከፍ ወይም ዝቅ ልትል የምትበቃው እኛ ልጆቿ የምንሰጠው የሥራ ፍሬ የሚጠቅም ወይም የማይረባ ሆኖ በሚገኝበት መጠን ነው። አሳባችንን የምናውለው በፍሬቢስ ነገር ላይ ብቻ የሆነ እንደሆነ አገራችን ከፍ ትላለች ብለን መመኘት ምንም መብት የለንም። ነገር ግን ዛሬ በዘመናችን ከፍ ያለውን ደረጃ የያዙት ሕዝቦች አገራቸውን ለመጥቀም ሲሉ የሚሠሩትን ሥራ አብነት በማድረግ ላንድ አገርና ላንድ ሕዝብ ዋኖቹ ጉዳዮች ምንድናቸው? ብለን እነሱን እየመረመርን የተሻለውን መልካም መንገድ ይዘን ለመሥራት ቆርጠን ብንነሣ መጭው ትውልድ የክብር፡ የኃይልና፡ የሲሳይ ዘመን ሆኖ ይጠብቀናል።

አባቶቻችን ይህችን የምንኮራባትን አገር ከነጻነቷና ከክብርዋ ጋር እንዳቆዩን ሁሉ፡ እኛ ደግሞ ባስታዋይነት ብንሠራ ለልጆቻችን የሚመኩበትን ሥራ ሠርተን አገራችን ከፍ ብላ የምትታይበትን ታሪክ እናወርሳቸዋለን። ሰው አላፊ፡ ጠፊ፡ ሟች ነው። አገርና ትውልድ ግን ለዘልዓለም ይኖራሉ።

ባሁኑ ሰዓት የዓለምን አካሄድ ስንመለከተው በሁለት ዓይነት ነገሮች ይመሰላል። አንድ ሰው በበቅሎ ተቀምጦ ጧት በአንድ ሰዓት ካቃቂ አይሮፕላን ማረፊያ ተነስቶ ወደ ምጽዋ ይጓዛል። በዚያው ሰዓት ከዚያው ቦታ አንድ ሌላ ሰው በአይሮፕላን ተሳፍሮ ይሄዳል። በበቅሎ የሚጓዘው ሰው ከሁለት ሰዓት በኋላ ለገዳዲ ይደርሳል፡ በአይሮፕላን የሄደ ሰው ግን በዚያው ሰዓት አሥመራ ይገባል። በበቅሎ የሚገሠግሠው መንገደኛ ማታ ምስር ምድር ሲገባ በአይሮፕላን የሄደ ሰው ካይሮ ይገባል። በበቅሎ የሚሄደው ሰው ወገቡ ደቆ፡ ጭኑ ጓጉሎ እግሩ ዝሎ ደክሞት ምስር ምድር ሰፍሮ ከተኛ በኋላ ጧት ጉዞዉን ወደ ደብረ ብርሃን ሲቀጥል፡ ሲነሳ በአይሮፕላን የተሳፈረው ሰው ሲሄድ ከዋለ በኋላ ምንም ድካም ሳይሰማውና የመልኩ ወዝ ሳይለወጥ እንቅልፍ መተኛትም ምንም ያህል ሳያስፈልገው፣ ብያስፈልገውም ጥቂት ተኝቶ ጧት ዓይኑን ሲገልጥ ፓሪስ ገብቶ ይገኛል። ይህ ነገር አሁን ላለንበት ዘመን ትልቅ ትምህርት የሚገኝበት ምሳሌ ነው። አገራችን ኢትዮጵያ ባመት ባመቱ በሥልጣኔ በኩል ስለምን አትራመድም? ብለን እናስባለን። ምክንያቱም ምን እንደሆነ አይገባንም።

ነገር ግን አስተውለን በንመለከተው ዋናው ነገር በሀሳብ ምክንያት ሆኖ እናገኘዋለን። ብዙ ሰዎች ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ቶሎ ወደፊት ለመረመድ የማትችለው በገንዘብ ምክንያት ነው ፣ ብዙ ገንዘብ ቢኖራት ኖሮ ብዙ መንገዶች

እየሠራች ብዙ ፋብሪካዎች እያቋቋመችና ሌላም አስፈላጊዎች የሆኑትን ነገሮችን እየገዛች እርምጃዋን ለማፋጠን ትችል ነበር ይላሉ። ይህ ነገር በከፊል እውነትን የያዘ ነው። ዳሩ ግን ዋናው ምክንያት ገንዘብ አይደለም። ገንዘብ ሰው የሠራው ነገር ነው እንጂ እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር አይደለም። ሰው ደግሞ ትልቅ ነገር ለመሥራት የሚችለው እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ ነው እንጂ የራሱ ሥራ በሆነው ገንዘብ በሚለው ነገር አይደለም። ሰው ሁሉን ነገር ሊሠራ የሚችልበት ከዝግዚአብሔር የተሰጠው መማሪያ አሳብ ይባላል። በዓለም ላይ የተሠሩትን ታላላቅ ሥራዎች በታሪክ ስንመለከታቸው ተሠርተው የተገኙት በሐሳብ ነው እንጂ በገንዘብ አይደለም። ሌላውን ሁሉ ነገር ትተን ባሁኑ ዘመን ከሰው ልጅ የተገኘውን አስደናቂ ሥራ ሆኖ የተቆጠረውን ቦንብ አቶሚክ ብንመለከተው እንደነ አይንሽታይን ወይም እንደ ፒየር ኪውሪ ከመሰሉት ሊቃውንት አንጎል ፈልቆ ወጣ እንጂ እንደነ ሮክፌለር የመሳሰሉት ሀብታሞች በገንዘባቸው ገዝተው ለዓለም አላበረከቱትም። ስለዚህ የሰው ልጅ ዋና ሀብቱ አሳቡ ነው። ገንዘብም የተፈጠረው በሰው አሳብ ነው!

ከፍ ብለን እንዳመለከትነው ምሳሌ ባሁኑ ዘመን ታላላቅ ሕዝቦች የሆኑት እንደዚያ በአይሮፕላን እንደተሳፈረው ሰው አሳባቸው በፍጥነት እየገሰገሰ ሩቅ ቦታ ደርሶ ዓለምን እየዞረ ሥራውን ሲፈጽም፡ አንዳንዶቹ ሕዝቦች ግን አሳባቸው ከሚኖርበት አገር ወይም አውራጃ ሳይወጣ ቀኑ ይመሻል። ስለዚህ ባሳብ የተቀደሙ በመሆናቸው ብቻ ወደ ኋላ ቀርተው ይኖራሉ። ከእነዚህ ሕዝቦች አንዱ እኛ ነን።

በንብረታችን፡ በግል ንሮአችን፡ በገዛ አገራችን ውስጥ ባሉብን ጉዳዮች ብቻ አሳባችን ከጧት እስከ ማታ እየተጠመደ እርስ በርሳችን በመጨቃጨቅ፡ በመናሸር፡ በመጣላትና በመታገል ብዛት ቀኑን ሙሉ ያሳባችንን ጉልበት ስንጨርስ እንውልና ማታ በመሸ ቁጥር ከባድ የሆነ ድካም እየተሰማን እንተኛለን። ሌሎቹ ሕዝቦች ግን ዕቀትና ጥበብ የተባለውን ዘመናዊ ጸጋ ላሳባቸው መሳርያ አድርገው ረጅም በሆነው አስተያየታቸው ዓለምን እየዞሩ ሰነፎች የሆኑትን ሕዝቦች እርስ በርሳቸው እያጣሉ ሀብታቸውን ወደቤታቸው እየሰበሰቡ ያገባሉ። የሰነፎች ዘር እየጠፋ እንዲሄድና የነሱ ትውልድ ግን እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ባሕር አሸዋ እየበዛ ሄዶ ዓለምን እንዲወርሳት ለማድረግ የሚችሉበትን መንገድ ለማዘጋጀት ተግተው ይሠራሉ። እስከዝያም ድረስ በሄዱበት ቦታ ሁሉ የተከበሩና የተፈሩ ናቸው። ይህንንም ሁሉ ሥራ የሚያከናውኑት ከፍ ባለ መንፈስ እየተመሩ ስለሆነ ድካም አይሰማቸውም። ሁልጊዜ የሚታዩት ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ ነው ፣ ተመልካች የሆነ ሰውም ምን ጊዜ ነው ሥራቸውን የሚሠሩ ብሎ ያስባል። ባጭሩ ድካም ሳይሰማው ጧት ካዲስ አበባ ተነስቶ እየተጫወተ ከተጓዘ በኋላ ማግሥቱ ጧት ፓሪስ የሚገባውን መንገደኛ ሰው ይመስላሉ፤ ያ በበቅሎ የሚጓዘው ምስኪኑ መንገደኛ ግን ካሰበበት ቦታ ከምፅዋ ለመድረስ ሁለት ወር ስለሚያስፈልገው በአይሮፕላን የሄደው ሰው መላ ዓለምን ዞሮ ከዋሽንግቶን፡ ከቶክዮ፡ ከፐኪን፡ ከኒውደሊና ከሲድኒ፡ ከሞስኮ፡ ከካይሮ ደርሶ የአመሪካንን፡ የጃፓንን፡ የሺናን፡ የሕንድን፡ የኦስትራልያን፡ የግብፅን፡ አገሮች ከጎበኘ በኋላ ጉዳዩን ሁሉ ፈጽሞ ተመልሶ አዲስ አበባ ይገባል።

ስለዚህ እኛ የተቀደምነው በማመላለሻ መማርያ ብቻ ሳይሆን ባሳብም ጭምር ነው። አገራችን ሃብታም ስለሆነች ብናውቅበት የምንፈልገውን ያህል ብዙ ገንዘብ ማግኘት እንችላለን። ያለንን ፍቅር ለመግለጥ የምንችለው የዘመናችን ሕዝቦች የሚዋጉበትን

የጦር መሣርያ ለመሥራት የምንችልበት ዘዴ ፈልገን በማግኘት መሆኑን ገና አልተረዳነውም።

በምንማረው ትምህርት ከዘመናዊ ሥልጣኔ ልንፈልገው የሚገባን ነገር የሚጠቅመንን ብቻ ለማግኘት ስለሆነ ራሳችንን የቻልን መሐንዲሶች፡ የፋብሪካ መኪና፡ አስኪያጆች፡ ሐኪሞች፡ የእርሻ ሥራ አዋቂዎች ሆነን ላገራችን የሚያስፈልጉትን ሥራዎች ሁሉ ራሳችንን ችለን ባዕድ ሳናስገባ ለመሥራት የምንችል ሆነን እንድንገኝ ያሻል። ባጭሩ ላንድ መንግሥትና ላንድ ሕዝብ ኑሮ አስፈላጊዎች የሆኑትን ሥራዎች ሁሉ ከነጮች እኩል በዘመናዊ ጥበብ ለማከናወን የምንችልበት መንገድ መፈለግ አለብን። እንግዲህ ይህን ሁሉ ነገር ለመፈጸም የምንችለው በማሰብ ብቻ መሆኑን እንወቀው። እንደርስበታለን የማለት እምነት በልባችን አሳድረን ባሳባችን ኃይለኞች ከሆንን ይህን ሁሉ ነገር ልንፈጽመው እንችላለን። አሳባችንን ኃይለኛ ልናደርገው የምንችል ደግሞ ጉልበታችንን እርባና ለሌለው ነገር ነገር ማባከናችንን ትተን እነዚህን ላገራችን ዋኖች ጉዳዮች የሆኑትን ነገሮች ብቻ ባሳባችን ውስጥ በማውጣትና በማውረድ የሚበጀውንም መንገድ ለማግኘት ስንል ለእነዚሁ ጉዳዮች አዲስ አሳብ እየሰጡን ሊረዱን የሚችሉትን መጻሕፍት በማንበብ ነው። ስንፍና ካላሸነፈን በቀር የምንፈልገውን ሁሉ በመጻሕፍት ውስጥ እናገኘዋለን። ትንኝ (ቢምቢ) ምግቧን ከአበባ ላይ ቀስማ ለሰው ልጅ የወባን በሽታና ሞትን ትሰጠዋለች። ንብ ደግሞ በበኩሏ ከአባባ ላይ ምግቧን ቀስማ ለሰው ልጅ ጣፋጭ የሆነውን ማር ትሰጠዋለች። ሰዎችም እንደዚሁ በመጽሐፍ ውስጥ ሊጠፉበት ወይም ሊለሙበት የሚችልበትን ትምህርት ስለሚያገኙበት የሚጠቅማቸውንና የሚጎዳቸውን እየመረጡ መቅሰም፡ ይህ ህልናቸውን ዳኛ አድርገው ሊፈጽሙት የሚገባ ተግባር ነው።

ሰው አስቸጋሪ የሆነ ሥራ ሊፈጽም በፈለገ ጊዜ ምሳሌ ወይም መዝገብ ወይም አብነት ሆኖ ሊያገለግለው የሚችል አንድ ነገር ሲያገኝ ያሰበውን ሥራ በቶሎ ለመፈጸም ቀላል ነገር ይሆንለታል።

አለዝያ ግን መንገዱ ጠፍቶበት በመደናበር ጊዜውን ይፈጃል። አገራችንን ልንጠቅማትና ልናገለግላት የምንችልበትን መንገድ ለማወቅ ብንፈልግ የጃፓን ታሪክ ከማንበብ የተሻለ ምንም ነገር አናገኝም። ወደ ኋላ ከቀሩት አገሮች ሁሉ ነጻነቷን ሳታስደፍር ለመሠልጠን የቻለች እሷ ብቻ ነች። በጥቂቱ ዓመታት ውስጥ በሥልጣኔ ራሷን የምትችልበትን መንገድ እቅድ (ፕላን) እንዴት አድርጋ እንዳዘጋጀችውና በአለው የምትሰጠን ምሳሌ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በማንኛውም ዘመን ወይም በማናቸውም አገር ተደርጎ የማይታወቅ ድንቅ ነገር ነው። የጃፓን ሕዝብ አገሩ ደሀ ነው። ሕዝቡ ግን አሳቡ ሩቅ፡ የሚያስተውል የመንፈስ ባለ ጸጋ በመሆኑ ብቻ ሁልጊዜ ራሱን ከፍ አድርጎ ለማሳየት ቻለ። ስለዚህ ታሪካቸውን በማንበብ ምሳሌ ሆኖ ልያገለግለን የሚችልና የመንፈስ ባለጸጎች የሚያደርጉን ብዙ ትምህርት እናገኝበታለን።

ይህንን ከፍ ያለ ተግባር ሲፈጽሙ ጃፓኖች ባለሥልጣኖቻቸው፡ መንግሥታቸው፡ ሕዝባቸው፡ ባንድ አሳብና ባንድ ዓይነት ምኞት የተቃኙ ሆነው በመታየት የውጭ ጠላት በስብከትም ሆኖ በሌላ በማንኛውም ነገር የሚገባበት ቀዳዳ ባለመስጠታቸው

ኅብረታቸው ብረት የለበሰ መሳርያ ሆኖ ተገኝቷል። ከሁሉም ይልቅ ደግሞ የጃፓን ታላላቅ ሰዎች ታሪካቸው፣ የሰውን መንፈስ ወደ ትልቅ ዓላማ የሚመራ አብነት ነው። እንግዲህ ለዚህ ሁሉ መድኃኒቱ ምንድነው? ብለን ስናስብ፣ ከኛ ካሁኖቹ ሰዎች ቀጥሎ አዲስ ትውልድ ውስጥም ስለ አገራችን ስለ ኢትዮጵያ የምንመኝላት ከፍ ያለው ምኞት በልባቸው ውስጥ አድሮ ላገር ጠቃሚዎች የሆኑትን ታላላቅ ሥራዎች ለመፈጸም የሚችሉ ሙሉ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች እንዲፈጠሩ ማድረግ የሚቻልበትን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ይህንኑም ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መንገዶች በመከተል ልንደርስበት እንችላለን።

በቴክኒክ ትምህርት ቤቶች የተማሩ ልዩ ልዩ ሥራዎች የሚያውቁ ሰዎች ቢኖሩን ኢትዮጵያን ኃይለኛና ሀብታም መንግሥት ለማድረግ የምንችልበት፣ ተቆጥሮ የማያልቅ ብዙ ሥራ ለመፈጸም እንችላለን። የአናጢነትን ሥራ አሳምረው የሚያውቁ ሠራተኞች ኢትዮጵያ ቢኖርዋት ኖሮ በእንጨት ሀብታም አገር ስለሆነች በእንጨት የሚሠሩ ልዩ ልዩ ዕቃዎች እየሠራች ለጎረቤቶቿ ለነግብፅ እየሸጠች ብዙ ሀብት ለማግኘት ትችል ነበር። አሁን ግን እንኳንስ ይህን ልታደርግ ወርቋን እያፈሰሰች ለራሷ እንኳ በውጭ አገር እንጨትና በውጭ አገር ሰዎች እጅ የተሠሩ የቤት ዕቃዎች ስትገዛ ትታያለች።

ራሳችንን እስከምንችል ድረስ ግን ከሁሉም የሚሻለው ዘዴ ባገራችን የሚጠቀሙት ነጋዴዎችና ባለ ኢንዱስቱሪዎች፣ ከኢትዮጵያውያን ጋር ካፒታላቻውን እኩል ለኩል እያደረጉ አብረው በባለአክሲዮንነት እንዲሠሩ ማስገደድ ነው።

እንደዚሁ አድርጎ ባለሥልጣን የሆነ በሥልጣኑ፣ ባለጸጋ የሆነ በገንዘቡ፣ ትምህርት ያለው በዕውቀቱ እየተረዳዱ ቢሠሩ አገራችን ትልቅ የምትሆንበትን የማያጠራጥረውን መንገድ ተከትለናል ለማለት እንችላለን። ሥልጣን፣ ገንዘብና ጥበብ ካልተረዳዱ ደግሞ ባሁኑ ሥልጣኔ ዘመን ፍሬ ያለው ሥራ ለመሥራት አይቻልም ይህንንም ስናደርግ አንድ ነገር ማሰብ አለብን። ለሰው ልጅ የሕይወቱና የኑሮው ዓላማዎች ሁለት ብቻ ናቸው። አንደኛ በነፍሱ በኩል መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት መጣጣር ሲሆን ሁለተኛው ግብ ደግሞ የተወለደባትን አገር በመንግሥታት መካከል ስትቀመጥ ልጆቿ በፈጸሙት ሥራ ለመመካት ችላ ከፍተኛ ደረጃ እንድትይዝ ለማድረግ መሥራትና መድከም ያለበት መሆኑን ማወቅ ያስፈልገዋል።

የዓለምን ጆግራፊ ገልጠን የእያንዳንዱን አገር ታሪክ እየመረመርን ስንመለከተው በዓለሙ ከፍል በሚገኙት በብዙ አገሮች በቅርብ ዘመን በድንቁርና ይኖሩ የነበሩ ስንት ሕዝቦች ዛሬ አውራጆቻቸውን የሚያገናኝዋቸው ብዙ መንገዶችና የባቡር ሐዲዶች እየዘረጉ፣ ትምህርት ቤቶችና ኢንዱስትሪዎች እያቋቋሙ የእርሻና ያታክልትን ሥራዎች በሰፊው እየሠሩ አገራቸውን በማልማትና በማበልጸግ፣ የሕዝቡ ቍጥር ከፍ ከፍ እያለ እንዲሄድ በማድረግም ማዕድኖቻቸውንም እያወጡ በመጠቀም ብዙ አዳዲሶች ከተሞች በመሥራትም ያገራቸውን መልክ ፈጽሞ ለውጠውት ይታያል።

ይህንንም ለማድረግ የበቁት ካገራቸው ልጆች ተክኒሲያኖች በማስተማራቸው ነው። ልጆቹ እንደዚህ አድርገው ራሳቸውን ችለው በመሥራት ሀብቷን እንዲሠራበት አድርገው ኢትዮጵያን ለዚህ መልካም ዕድል የሚያበቋት የሚያሳምርዋትና የሚያበልጽጓት መቼ ነው?

---

አንባቢ ሆይ ከላይ የቀረበውን የአቶ ከበደ ሚካኤል ጥያቄ ለመመለስ ተዘጋጅተሃል ወይ? አቶ ከበደ ሚካኤል ጃፓን እንደምን ሠለጠነች የጻፉት ከዓርባ ዓመታት በፊት ነው፣ ይዘቱና ትንታኔው እንዲሁም የደራሲው ክስተት ግን ለአሁኑ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አግባብነት ያለው ከመሆኑም በላይ ፖለቲካውን አስመልክቶ ደግሞ በሚገርም ሁኔታ የሚያንጸባርቅ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ታድያ ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል፣ ላገራችን በግል ሆነ በስብስብ ምን ማድረግ እንችላለን? እርስ በራሳችን እየተናቆርን ታሪካችንን እናጉድፈው ወይስ ልዩነታችንን አስወግደን ላንድ ዓላማና ለላቀ አንድነት እንሰለፍ? እነዚህን ጥያቄዎች መልሰን በግብር መተርጐም ከጀመርን በኋላ ላገራችን የሚበጅ የአንድነት፡ የልማትና የመሠረታዊ ለውጥ መንገዶችን ቀየስን ማለት እንችላለን። አለዛ አሁን ባለው ውጥንቅጥ የወጣ የመነካጠልና የመፍረክረክ ፖለቲካ ወደ ባሰ መበታተን ሊያመራን ይችላል። እጅግ በጣም መጠንቀቅ አለብን። ስለሆነም ታሪካዊ ግዴታችንን መዘንጋት የለብንም።

**መልካም ዕድል ለኢትዮጵያና ባንድነታቸው ለጸኑ ዜጎችዋ!**

All Rights Reserved. Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA), Inc. 2011. Dr. Ghelawdewos Araia can be contacted for educational and constructive feedback via dr.garaia@africanidea.org